# Grenfell Tower: September 2025 community update -Amhraic / አማርኛ

**ግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower)፦ የሴፕቴምበር 2025 የማህበረሰብ ወቅታዊ**

ግሬንፌል ታወርበአደጋው በጣም ለተጎዱት ሰዎች ጥልቅ ግላዊ ትርጉም እንዳለው እና መሬቱ ለቤተሰቦቹ የተቀደሰ እንደሆነ እንገነዘባለን። መንግስት እና ኮንትራክተሮቻችንግሬንፌል ታወርን በክብር እና በጥንቃቄ ለማፍረስ እንዴት እንደሚጀምሩ መረጃ እና ከእኛ ጋር ለመነጋገር ያሉላችሁ ዕድሎችን እያጋራን ነው።

በዚህ አዲስ መረጃ ውስጥ ስለሚከተሉት ተጨማሪ ማወቅ ይችላሉ፦

- **ግሬንፌል ታወርን በጥንቃቄ ለማፍረስ ስለሚሠራ ሥራ**
- **የአካባቢ አስተዳደር ዕቅዶችን ስለማጋራት**
- **እንዴት እኛን ማነጋገር እንደምትችሉ**
- **ስለጤና እና ደህንነት**

## ግሬንፌል ታወርን በጥንቃቄ ለማፍረስ ስለሚሠራ ሥራ አዲስ መረጃ

መንግስት በቦታው ላይ የሚሠሩ ሥራዎች በከፍተኛ ደረጃ እንዲከናወኑ እና የህንፃውን ጠቀሜታ ባከበረ መልኩ መሠራታቸውን ለማረጋገጥ ቁርጠኛ ነው። ዘዴው በአቅራቢያው በሚኖሩ፣ በሚማሩ እና በአቅራቢያ በሚሠሩ እንዲሁም አክብሮታቸውን ለመግለጽ ወደ አካባቢው በሚመጡት ላይ የሚያስከትለውን ረብሻዎች ለመቀነስ የተቀየሰ ነው።

በጁላይ ወር ዋናው ተቋራጭ (DUK) ታወሩን በጥንቃቄ ለማፍረስ ሥራውን እንዴት እንደሚያከናውን እና የታወሩን ቁሳቁሶች እንዴት በአክብሮት እንደምናሳርፍ መረጃ አጋርተናል። ይህንን መረጃ ወደሚከተለው በመሄድ ማንበብ ትችላላችሁ፦ [Grenfell Tower site update - GOV.UK](Grenfell Tower site update - GOV.UK).

በበጋው ወቅት DCUK ክሬን መትከል እና ለሁለተኛ ባነር መቅረጽ ጨምሮ የዝግጅት ስራዎችን አከናውኗል። ሁለተኛው ባነር ተተክሏል፣ እንዲሁም የላይኛው ባነር ተወግዷል። ሁለተኛው ባነር ከማታ ጀምሮ እስከ ምሽቱ 11 ሰአት ድረስ እየበራ ነው። የእጽዋት ክፍል (ማሞቂያ እና የውሃ ማጠራቀሚያ ያለው) ከግንቡ አናት ላይ የማስወገድ ስራ አልቋል። በመኖሪያ ፎቆች ላይ ሥራ አሁን ይጀምራል። ስራው (ከህንፃው አናት ጀምሮ) ወለሉን በስሱ እየገፋ ሲሄድ የመጠቅለያው ቁመቱ ቀስ በቀስ እየቀነሰ ነው። ስራው በ2027 ይጠናቀቃል ብለን እንጠብቃለን።

## የአካባቢ አስተዳደር ዕቅዶችን ማጋራት

በጁላይ ወር፣ ረብሻን ለመቀነስ እና በተቻለ መጠን ጥንቃቄ እንዲደረግ የአየር ጥራትን፣ ጫጫታን እና

የትራፊክ ማኔጅመንትን እንዴት እንደምንቆጣጠር እንዲሁም እንደምናስተዳድር መረጃ አጋርተናል።

ለማህበረሰብ የሚሰጥ ወቅታዊ መረጃን እዚህ ማንበብ ችላላችሁ፡-
የግሬንፌል ታወር ጣቢያ ወቅታዊ መረጃ፡- የአካባቢ ቁጥጥር - GOV.UK

ይህ ወቅታዊ መረጃ የአየር ጥራት፣ የአቧራ እና የጫጫታ መጠንን ስለምንቆጣጠር እና ገደቦች ከተጣሱ ምን እርምጃዎችን እንደምንወስድ የበለጠ መረጃ ይሰጣል።

የአየር ጥራት፣ የጫጫታ እና የንዝረት የቁጥጥር መረጃዎች በየወሩ ይታተማሉ።

የሚከተሉትን ዕቅዶች እያዘጋጀን ሲሆን ከእናንተ ጋር ለመውያየት ደስተኞች ነን፡-

- የአየር ጥራት እና አቧራ ቁጥጥር ዕቅድ (AQDMP)
- የጫጫታ እና የንዝረት ቁጥጥር ዕቅድ (NVMP)

ዕቅዶቹ ለDUK የተዘጋጁት በአውሮፓ የአካባቢ ጥበቃ ቁጥጥር እና አማካሪ (EEMC) ሲሆን ይህም በግንባታ ሥራ ላይ በአካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ነው።

**የጫጫታ እና የንዝረት ቁጥጥር**

NVMP በጣቢያው ላይ የጫጫታ እና የንዝረት መቆጣጠሪያዎችን ዝርዝር እና ስልታዊ አቀማመጥ ይዘረዝራል።

ቁልፍ ነጥቦች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- በጣቢያው በደቡብ በኩል ሁለት የንዝረት መቆጣጠሪያዎች ተተክለዋል።
- አጠቃላይ ሽፋን ለመስጠት እና ከአካባቢ እና ከግንባታ ጋር በተያያዙ የጫጫታ ደረጃዎች ላይ የእውነተኛ ጊዜ መረጃዎች እንዲሰበሰቡ ለማስቻል ሶስት የጫጫታ መቆጣጠሪያዎች በጣቢያው ወሰን ዙሪያ ተቀምጠዋል።
- የእነዚህ መቆጣጠሪያዎች መተከል ከምርጥ ተሞክሮ እና የቁጥጥር መመሪያ ጋር በተጣጣመ መልኩ ንቁ ቁጥጥር እንዲኖር እና ተፅዕኖን በወቅቱ ለመቀነስ የተነደፈ ነው።
- በታው ለጫጫታ ከፍተኛ ስጋት እንዳለው ተገምግሟል፣ እናም NVMP በምላሹ የተዘጋጀውን መቀነሻ ዕቅድ ይዘረዝራል። ይህ ዕቅድ ሁለቱንም የመቀነሻ እርምጃዎችን እና ከለንደን ባለስልጣናት የጫጫታ አክሽን ፎረም (LANAF) መመሪያ ጋር የተጣጣሙ የምርጥ ተሞክሮ ፕሮቶኮሎችን ያካትታል። እነዚህ እርምጃዎች የተነደፉት በአቅራቢያው በሚኖሩ፣ በሚሠሩ እና በሚማሩ ላይ የጫጫታ ተፅእኖን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመቀነስ እና የሚመለከታቸው ደረጃዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ነው።
- NVMP የጫጫታ እና የንዝረት ደረጃዎችን እንዲሁም እነዚያ ደረጃዎች ከተጣሱ የሚወሰዱት እርምጃዎችን ይዘረዝራል።

**የአየር ጥራት ቁጥጥር**

የአየር ጥራት እና አቧራ ቁጥጥር ዕቅድ (AQDMP)፣ የአየር ጥራት ቁጥጥር ኢንስቲትዩት (IAQM) እና የግሬተር ለንደን ባለስልጣን (GLA) ምርጥ ተሞክሮዎችን ጨምሮ የአየር ጥራት ቁጥጥርን የሚያሳውቁ የህግ ማዕቀፎችን እና መመሪያዎችን ያስቀምጣል።

**ቁልፍ ነጥቦች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦**

- መቆጣጠሪያ ቦታዎች፦ አምስት የአየር ጥራት መቆጣጠሪያዎች እስትራቴጂያዊ በሆነ መንገድ የንፋስ አቅጣጫንያንፀባርቁ እና በ IAQM መመሪያ መሠረት በጣቢያው ወሰን ላይ ተተክለዋል።
- የሚገመተው ተጽዕኖ፦ በ AQDMP ውስጥ በተዘረዘሩት የመቀነሻ እርምጃዎች፣ ከIAQM እና GLA መመሪያ ጋር በተጣጣመ መልኩ አቧራ የሚያመነጩ እንቅስቃሴዎች ቀሪ ውጤት ጉልህ ላይሆን እንደሚችል ተንብዮአል።
- የማስጠንቀቂያ እና ምላሽ ፕሮቶኮሎች፦ ዕቅዱ የተወሰኑ ደረጃዎች ከተገኙ የሚወሰደውን እርምጃ ያብራራል፣ እንዲሁም የተወሰነ ገደብ ካለፉ የጣቢያው ሠራተኞች ምክንያቱን የሚመረምሩ ሲሆን ተጨማሪ የመቀነሻ እርምጃዎች እንደ አስፈላጊነቱ ይተገበራሉ።

የዩናይትድ ኪንግደም (UK) የጤና ጥበቃ ኤጀንሲ (UKHSA) ሥራ በሚካሄድበት ጊዜ በግሬንፌል ታወር አካባቢ ያለውን የአየር ጥራት መገምገም እና መከታተሉን ይቀጥላል። የአየር ጥራት ሪፖርቶች በየወሩ መታተማቸውን ይቀጥላሉ። የቅርብ ጊዜ ሪፖርቱን እዚህ ማንበብ ትችላላችሁ፦ የግሬንፌል ታወር የእሳት ቃጠሎን ተከትሎ የአካባቢ ቁጥጥር - GOV.UK

**እንዴት ከእኛ ጋር እንደምትነጋገሩ ወይም የበለጠ ለማወቅ**

መረጃ ለእናንተ በሚጠቅም መንገድ ልናካፍላችሁ እንፈልጋለን። እባክዎን ከስራዎቹ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሉዎት ወይም እኛን ለማነጋገር ማመቻቸት ከፈለጉ ያነጋግሩን። የኢሜል አድራሻችንGrenfellTowerSite@communities.gov.ukነው።

በመጪዎቹ ወራት መደበኛ ወቅታዊ መረጃዎችን እና መረጃዎችን www.gov.uk/grenfell-community-updates ላይ ማካፈላችንን እንቀጥላለን (ወይም ከታች ያለውን የQR ኮድ ስካን አድርጉ። ለኢሜል ማሳወቂያዎች መመዝገብም ትችላላችሁ። ከፈለጉ መደበኛ ዝማኔዎቻችንን በቀጥታ ወደ እርስዎ ኢሜይል መላክ እንችላለን። መረጃዎችን በዚህ መንገድ እንድናጋራችሁ ከፈለጋችሁGrenfellTowerSite@communities.gov.uk ላይ አነጋግሩን።

ስለ ሥራው ለመወያየት፣ ስጋቶችን ለማጋራት እንዲሁም በመደበኛ ስብሰባዎቻችን ላይ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ባለስልጣናትን እና የእኛን ዋና ስራ ተቋራጭ ማግኘት ትችላላችሁ። ለእርስዎ ለሚስማማ እና ምቹ በሆነ ሰዓት፣ ቀን እና ቦታ በግልም ሆነ በቡድን ከእርስዎ ጋር ለመነጋገር ፈቃደኛ ነን።

**የጤና እና የጤንነት ድጋፍ ከፈለጉ** ታወሩን በጥንቃቄ ለማፍረስ ስሜታዊ እና አካላዊ ደህንነት ድጋፍ ለሟች ቤተሰቦች፣ በሕይወት ለተረፉ እና በቅርብ ማህበረሰብ ውስጥ ላሉ ነዋሪዎች መደረጉን ቀጥሏል።

ማንኛውም የጤና ችግር ካለባችሁ፣ እባካችሁን GPያችሁን አነጋግሩ።

ከአንድ ሰው ጋር መነጋገር ከፈለግአችሁ፣ የሚከተሉትን ማድረግ ትችላላችሁ፦

- ወደ Grenfell Wellbeing አገልግሎት በ 020 8637 6279 (ከ8am እስከ 8pm፣ በየቀኑ) ደውሉ።
- በድንገተኛ አደጋ ጊዜ፣ ለCNWL Single Point of Access ምክር መስመር በ 0800 0234 650 ደውሉ (በቀን 24 ሰዓት፣ በሳምንት ሰባት ቀን ክፍት ነው)
- ኢሜል፡- grenfell.wellbeingservice@nhs.net
- ለተጨማሪ መረጃ: www.grenfellwellbeing.cnwl.nhs.uk ን ጎብኙ

ስላሉ አገልግሎቶች የቅርብ ጊዜ መረጃ እና ዝርዝሮችን ለማግኘት www.grenfell.nhs.ukጎብኙ።

በግሬንፌል ታወር ላይ የቅርብ ጊዜ ምእረጃዎችን ለማግኘትና ለኢሜል ማሳወቂያዎች ለመመዝገብ፣ እባክዎን ወደሚከተለው ድረገጽ ይሂዱ፡- www.gov.uk/grenfell-community-updates ወይም ከታች ያለውን የQR ኮድ ስካን አድርጉ።

ለግሬንፌል ታወሩ አደጋ ምላሽ በመስጠት ስለምናደርገው ሥራችን ወቅታዊ መረጃዎችን እንዴት ማግኘት እንደሚትመርጡ ለማወቅ በቀጥታ ከእናንተ መስማት እንፈልጋለን። ከፈለጋችሁ፣ የእኛን ፈጣን የግብረመልስ ቅጽ በመሙላት የእናንተን እይታዎች ማጋራት ትችላላችሁ፡- የግሬንፌል ማህበረሰብ፡- የግንኙነት ግብረመልስ ቅጽ - GOV.UK

**□ግሬንፌል ታወር ጣቢያ አስተዳደር ቡድን**

**የቤቶች፣ ማህበረሰቦች እና የአካባቢው አስተዳደር ሚኒስቴር**